# በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃትን ለመከላከል የወጣ መመሪያ

INJIBARA UNIVERSITY

እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ

2010 ዓ.ም

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

## መግቢያ

በኢፌዴሪ ህገ መንግስት እና ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው እና ካፀደቀቻቸው በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች መሠረት ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት የሰብአዊ ጥሰት በመሆኑ እንዲሁም ማንኛውም ሰው በነፃነት የመማር፣ መልካምና ምቹ የመማሪያ አካባቢ የማግኘት መብት ያለው በመሆኑ፣

ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት በሁለቱም ፆታዎች ላይ የሚፈፀም ተግባር ቢሆንም፣ በተለይ የችግሩ ተጋላጭ የሆኑት ሴቶች በመሆናቸው፣ ይኸም የሴቶችን የትምህርት ተሣትፎ ብቃት ውጤታማነት የሚያቀጭጭ በመሆኑ በሀገሪቱ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ባሕላዊ እድገትን ልማት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያለው በመሆኑ፣

በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ሊፈፀሙ የሚችሉ ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ለመከላከል፣ ለመቀነስና ብሎም ለማጥፋት እንዲሁም የጥፋት ድርጊት ፈፃሚዎች ላይ ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ አሁን በስራ ላይ ባለው የኢፌድሪ የወንጀል ሕግ እና ሌሎች የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የዲሲኘሊን መመሪያዎች ባሻገር ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት በተጠናከረ መልኩ ለመከላከል፣ ለመቀነስ ብሎም ለማጥፋት ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት በዝርዝር የሚዳስስ ራሱን የቻለ ፀረ-ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት መመሪያ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የኢፌድሪ ትምህርት ሚኒስቴር በትምህርት ተቋማት የሚፈፀመውን ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ለመከላከል ያወጣውን መመሪያ መሠረት በማድረግ ከዩኒቨርሲቲው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ በማስፈለጉ የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ሴኔት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 49 እና በፌዴራል ዩኒቨርሲቲዎች የሚኒስትሮች ደንብ ቁጥር 201/2003 አንቀጽ 6(1)(ለ) በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

F.D.R.E Ministry Of Education
Injibara University

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሳንና ጥቃት ለመከላከል የወጣ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. የተፈፃሚነት ወሰን

1. ይህ መመሪያ በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ በሚገኙ የአካዳሚክ ማህበረሰብ፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ የኮንትራትና የቀን ሠራተኞች መካከል በትምህርት ተቋሙ ቅጥር ውስጥ ለሚፈፀሙ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ፈፃሚዎች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ ሆኖም ከዩኒቨርሲቲው ቅጥር ግቢ ውጪ ቢሆንም ለዩኒቨርሲቲው ስራ እነዚህ ማህበረሰቦች ሥራ ላይ ከሆኑ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡
2. ይህ መመሪያ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሚቀጠሩ ተጋባዥ መምህራንና የኩንትራት ሠራተኞችም ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 3. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፣

1. **"ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት"** ማለት በፌደራል መንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 አንቀጽ 2(13) ስር የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባልና የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪና የኮንትራት ሠራተኛ በሌላ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባልና የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪና የኮንትራት ሠራተኛ ከሌላኛው ፈቃድ ውጪ ወይም ወሲባዊ ጥያቄን እንደ ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጥ (Quid Pro Quo) የሚቀርብ የወሲብ ጥያቄ ወይም ሌላ ወሲባዊ ይዘት ያለው የቃል ወይም የአካል ንኪኪና በአካላዊ እንቅስቃሴ ምልክት መስጠት ተግባር ወይም በአካል ወይም በስነ አእምሮ ላይ የሚፈፀም ጥቃት ሆኖ በዚህ መመሪያ ክፍል ሁለት ላይ የተዘረዘሩትን ያካትታል፡፡
2. **"ዩኒቨርሲቲ"** ማለት እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡
3. "አካዳሚክ ማህበረሰብ፣ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም" የሚሉት ቃላት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ቁጥር 650/2001 አንቀጽ 2 እና በዩኒቨርሲቲው የሴኔት ሌጅስሌሽን ላይ የተሰጣቸው ትርጓሜ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

4. **"ፕሬዝዳንት"** ማለት የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንት ነው፡፡

5. **"ማህበራዊ አገልግሎት"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 8(2) መሠረት ቀላል ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ተግባር በፈፀመ ተማሪ ላይ የሚፈፀም የቅጣት አይነት ሲሆን፣ ቅጣቱ በዩኒቨርሲቲው የውስጥ ደንብ በተለየ ሁኔታ ካልተቀመጠ በስተቀር የአካባቢ ጽዳት፣ አትክልት መንከባከብ ወይም የመመገቢያ ቦታዎችንና እቃዎችን ማጽዳት እና ሌሎች ተመሣሣይ ተግባራትን የሚያካትት ነው፡፡

6. **"ኮሚቴ"** ማለት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 የተቋቋመው የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ነው፡፡

7. **"ተገቢው ጥበቃ"** ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት የኮሚቴ አባል ሆኖ እንዲሰራ ለተመደበ ወይም ክስ ላቀረበ ወይም ምስክርነት ለሰጠ የአካዳሚክ፣ ተማሪ ማህበረሰብ አባል ወይም ለድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ የሚሰጥ ጥበቃ ሆኖ የሚከተሉትን እርምጃዎች ያካትታል፤

   ሀ) ጥበቃ የሚያስፈልገው ተማሪ በሆነበት ጊዜ መምህሩ /የመማሪያ ክፍሉ እንዲለወጥለት ወይም ፈተናው በሌላ አራሚ እንዲታረምለት ማድረግን፣

   ለ) ጥበቃ የሚያስፈልገው መምህር ወይም ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ከሆነ የስራ ኃላፊው እንዲቀየርለት ወይም ወደ ሌላ የስራ ክፍል ወይም የስራ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከነዚህ እርምጃዎች ጋር ተመሳሳይነትና ሌላ ተገቢነት ያለው እርምጃን፣የሚያካትት ነው፡

8. **"መመሪያ"** ማለት በዩኒቨርሲቲው ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ለመከላከል የወጣ መመሪያ ማለት ነው፡፡

9. በዚህ መመሪያ ውስጥ በሴት ፆታ የተገለፁት ቃላቶች ለወንድ ፆታም ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አይነቶች</u>

4. <u>የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ተግባራት ዓይነቶች</u>

በዚህ መመሪያ አንቀጽ 3(1) የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃቶች የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ተግባራት የሚከተሉትን ያካትታል፤ በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ቀላል ጾታዊ ትንኮሳዎችና ጥቃት የፈፀመ ወይም እንዲፈፀም የተባበረ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባልና የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪና የኮንትራት ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 7-12 የተመለከቱት የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድበታል፡፡



ብርሃኑ በላይ እቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

F.D.R.E Ministry Of Education Injibara University

## 5. ቀላል የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አይነቶች

በዚህ መመሪያ መሰረት የሚከተሉት ድርጊቶች ቀላል የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አይነቶች ናቸው፡፡

1. አስነዋሪ በሆነ መልኩ ወሲብ ቀስቃሽ አካላትን በተለይም ተፈጥሯዊ የተራክቦ የሰውነት ክፍሎችንና የጾታ መገለጫዎችን አጋልጦ ማሳየት፣
2. የሌላውን ወሲባዊ ፍላጐት ሊያነሳሱ የሚችሉ ፅሁፎችና መጽሔቶችን በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለሌሎች ያለፈቃዳቸው ማሳየት፣
3. ወሲብ አዘል ሁኔታን የሚያንፀባርቁ ቀልዶች፣ ቧልቶች፣ አስተያየቶች፣ ጥያቄዎች፣ ገጠመኞች እና ሌሎች ተመሳሳይ ተግባራትን ከሌላው ሰው ፈቃድ ውጪ ፈፅሞ መገኘት/መናገር/፣
4. ወሲብ አዘል በሆነ ሁኔታ ጾታን ማጥላላት፣ ማናናቅና ማንኳሰስ፣
5. በግድግዳ ላይ ወይም በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ ለምሳሌ በሞባይልና በመሳሰሉት የወሲብ ምስል፣ የጽሁፍ መልእክትና ፎቶ ግራፍ ያለአንዱ ወገን ፈቃድ ለሌላ ሰው ማሳየት ወይም ማስተላለፍ፣
6. ለወሲብ በሚያነሳሳ መልኩ የአካል እንቅስቃሴ ለሌላ ወገን ማሳየት፣
7. የአንድ ሰው ፆታ ወይም ተክለ ሰውነት ወይም አለባበስ የተመለከቱና ወሲባዊ ተፈጥሮ ያላቸው አስተያየቶች፣ ነቀፌታዎች፣ ያልተፈለጉና አዋራጅ መገለጫዎችን፣ ቁጣ ቀስቃሽ ቅፅል ስሞችን መጠቀም፣
8. ተግባር ተኮር ትምህርቶች በሚሰጥበት ወቅት ወሲባዊ ድርጊትን በሚያመላክት መልኩ የአካል እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ወይም የቃል አስተያየቶችን መስጠት፤

## 6. ከባድ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ዓይነቶች

1. በኤሌክትሮኒክስ መሣሪያ፣ በድህረ-ገጽ ወይም በሌሎች መሰል መንገዶች የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባልና የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪና የኮንትራት ሠራተኛን ምስል በመጠቀምና በማስመሰል የሌላን ሰው ወሲባዊ ህይወት የሚያጋልጡና የሚያንቋሽሹ ተግባራትን መፈጸም፣ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪ ወይም የኮንትራት ሠራተኛን አካላት በመዳሰስ፣ በመተሻሸት፣ ያለፈቃድ በመሳም ወይም ሆን ብሎ ሌሎች ለወሲብ የሚገፋፉ የሰውነት አካል ግንኙነት መፍጠር፤
2. አንድን ሰው በማንኛውም ቦታ በመከታተልና በነፃነት የመንቀሳቀስ መብትን በመገደብ በግለሰቧ/በግለሰቡ ለይ የስነ ልቦና ጫና ማሳደር፤



ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

F.D.R.E Ministry Of Education
Injibara University

3. ለትምህርት ውጤት ሆነ ለተለያዩ የትምህርት ተግባራትና አገልግሎቶች ወሲብን እንደቅድመ ሁኔታ አስቀምጦ መጠየቅ፣
4. ወሲብ አዘል ድርጊቶችን በማስገደድ ለመፈፀም በማሰብ የትምህርት መሣሪያዎችና ዋጋ ያላቸውን ንብረቶች መቀማትና መደበቅ፣
5. ቀላል የጾታዊ ትንኮሳ በመፈፀም በተወሰደበት የቅጣት እርምጃ ባለመታረም ከሁለትና ከዚያ በላይ ቀላል የጾታዊ ትንኮሳዎችን መፈፀም፣
6. አስገድዶ መድፈር፣
7. በዚህ አንቀጽ የተመለከቱትን ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃቶች አይነቶች እንዲፈጸም የተባበረ ወይም ያደመ፣
8. በአካል ጉዳተኞች ላይ የሚፈጸም ቀላል ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት በከባድ የጾታዊ ትንኮሳ ተግባራት ከተመለከቱት የጥፋት ድርጊቶች ጋር እኩል ክብደት ይኖራቸዋል፤
9. በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ከባድ የጾታዊ ተንኮሳና ጥቃት ዓይነቶች የፈጸመ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባልና የተጋባዥ መምህራን ወይም የአስተዳደር ድጋፍ ሰጪና የኮንትራት ሠራተኛ እንደጥፋቱ ክብደት በዚህ መመሪያ ከአንቀጽ 7-12 የተመለከቱት የቅጣት እርምጃዎች ይወሰድበታል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የዲሲፕሊን እርምጃዎችና አወሳሰድ

### 7. የሚወሰዱ የዲስኘሊን እርምጃዎች

ማንኛውም የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም ድጋፍ ሰጪ ሠራተኛ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አይነቶች ከፈጸመ በሌሎች ህጎች የተመለከቱት ቅጣቶች እንደተጠበቁ ሆኖ እንደጥፋቱ ክብደት ከሚከተሉት የቅጣት አይነቶች አንዱ ተፈጻሚ ይደረግበታል፡፡ ሆኖም ድርጊቱ በሌሎች የዩኒቨርሲቲው መመሪያዎች የተሸፈነ ከሆነ ግን የከበደውን ቅጣት የያዘ የዲሲኘሊን ህግ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

### 8. ቀላል ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አይነቶች በፈፀሙ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ የዲሲኘሊን እርምጃ

1. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ እና (6) ስር ለተዘረዘሩት ቀላል ጥፋቶች ከተግሳጽ/የቃል ማስጠንቀቂያ እስከ ጽሁፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፣



ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

2. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5)፣ (7)፣ እና (8) ለተዘረዘሩት ቀላል ጥፋቶች በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተዘረዘሩት በተጨማሪ የአንድ ወር ተከታታይ የማህበራዊ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

9. ከባድ ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ዓይነቶች በፈፀሙ ተማሪዎች ላይ የሚወሰድ ከባድ የዲስኘሊን እርምጃ

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3)፣ (4) እና (7) ስር የተዘረዘሩትን ከባድ የዲስፕሊን ግድፈቶች የፈጸመ ከአንድ ሴሚስተር እስከ አንድ ዓመት ከትምህርት መታገድ፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) ስር የተዘረዘረውን ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት የፈጸመ ከአንድ ዓመት እስከ ሁለት ዓመት ከትምህርት መታገድ፣
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (6) ላይ የተዘረዘሩትን ከባድ ጥፋቶች የፈጸመ ከትምህርት ገበታው የሚሰናበት ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሰረት ጥፋት የፈጸመው ተመራቂ ተማሪ ሲሆን የትምህርት ማስረጃው ለሦስት ዓመት ታግዶ ይቆያል/አይሰጠውም፡፡

10. በቀላል ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ዓይነቶች በፈፀሙ የአካዳሚክ ሰራተኞች ላይ የሚወሰድ የዲስኘሊን እርምጃ

1. ተግሳጽ/የቃል ማስጠንቀቂያ፣
2. የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፣
3. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ እና (6) ስር ለተዘረዘሩት ቀላል ጥፋቶች በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ወይም በተናጥል የሚፈጸም እስከ 10 ቀናት የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፤
4. በዚህ መመሪያ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (4)፣ (5)፣ (7)፣ እና (8) ለተዘረዘሩት ቀላል ጥፋቶች በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ወይም በተናጥል የሚፈጸም ከ10 እስከ 15 ቀናት የሚደርስ የደመወዝ ቅጣት፤
5. ተጋባዥ መምህራን፣ የቀንና ኮንትራት ሠራተኛን በሚመለከት በመመሪያው አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ እና (6) ስር ለተዘረዘሩት ቀላል ጥፋቶች በዚህ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ከተዘረዘሩት በተጨማሪ ከዩኒቨርሲቲው የሚያገኘውን ጊዜያዊ የገንዘብ ጥቅማጥቅም እንዲታገድ ማድረግ፤

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

11. <u>ከባድ ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ዓይነቶች በፈፀሙ የአካዳሚክ ሰራተኞች ላይ የሚወሰድ የዲሲኘሊን እርምጃ</u>

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3)፣ (4) እና (7) ስር የተዘረዘሩትን ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈቶች የፈጸመ የሶስት ወር ደመወዝ መቀጮ፣
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (5) ስር የተዘረዘረውን ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈት የፈጸመ ካለበት የደመወዝ ደረጃ ለአንድ አመት በሚቆይ ቅጣት እስከ ሁለት ደረጃ ዝቅ ማድረግ፣
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) እንደተጠበቀ ሆኖ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (6) ላይ የተዘረዘሩትን ከባድ ጥፋቶች የፈጸመ ከሥራ የሚሰናበት ይሆናል፤
4. ተጋባዥ መምህራን፣ የቀንና ኮንትራት ሠራተኛን በሚመለከት በመመሪያው አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (2)፣ (3)፣ (4) (5) እና (7) ስር የተዘረዘሩትን ከባድ የዲሲፕሊን ግድፈቶች የፈጸመ ከሆነ ከላይ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 5 የተቀመጠው ቅጣት እንደተጠበቀ ሆኖ ጥፋተኛውን ከስራው እንዲታገድ ማድረግ፤ ከዚህ በተጨማሪ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (6) ላይ የተዘረዘሩትን ከባድ ጥፋቶች የፈጸመ ከሆነ ከሥራ የሚሰናበት ይሆናል።

12. <u>በአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ</u>

ዩኒቨርሲቲዉ ውስጥ የሚሰሩ የአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ላይ የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃን በሚመለከት በፌዴራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 እና በፌዴራል መንግስት ሠራተኞች የዲሲፕሊን አፈፃፀምና የቅሬታ አቀራረብ ስነ ስርዓት ደንብ ቁጥር 77/94 መሠረት ያለው አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ ስለ ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት የተቀመጡ የቅጣት አይነቶችን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት በተቋቋመው የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ በሚቀርበው የውሣኔ ሀሣብ መሠረት በአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ይወሰናል።

13. <u>የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ አወቃቀር</u>

የጾታዊ ትንኮሳ አጣሪ ኮሚቴ ሰባት አባላት የሚኖሩት ሆኖ አባላቱም የሚከተሉት ናቸው።

1. የዩኒቨርሲቲው የስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ኃላፊ/ ሰብሳቢ፣
2. የዩኒቨርሲቲው ሴት ተማሪዎች ማህበር ተወካይ /በሴት ተማሪዎች ወይም በመምህራን የተመረጠች ተወካይ/፣
3. የተማሪዎች ህብረት ኃላፊ /ተወካይ፣

ዶ.ሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

4. የዩኒቨርሲቲው መምህራን ማህበር ሰብሳቢ/ተወካይ፣
5. የተማሪዎች ዲን/ የስራ ሂደት ባለቤት፣
6. የህግ አገልግሎት ኃላፊ/ተወካይ፣
7. በአስተዳደር ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች የሚመረጥ አንድ ተወካይ ሲሆኑ የኮሚቴው አወቃቀር የጾታ ስብጥርን ያማከለ መሆን አለበት፡፡

14. **የአባላት መመዘኛ**

ማንኛውም የኮሚቴ አባል፣

ሀ) በመልካም ስነ-ምግባር የተመሰገነ፣

ለ) የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ተግባር ትንኮሶ ወይም ጥቃት ፈጽሞ ያልተቀጣ፣

ሐ) ቢያንስ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ ለአንድ ዓመት ያገለገለ መሆን አለበት፡፡

15. **የኮሚቴው ሥልጣንና ተግባር**

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 እና 22 (1) መሠረት በዩኒቨርሲቲው ውስጥ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት ጥፋት ድርጊት ተፈጽሞብኛል የሚል አቤቱታ ሲቀርብለት የመመርመርና ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ወይም ለፕሬዝዳንቱ የውሣኔ ሀሣብ የማቅረብ፣
2. ኮሚቴው አቤቱታዎችን ሲመረምር አቤቱታ አቅራቢን፣ተከሳሽን ወይም ምስክሮችን የመጥራትና የመስማት፣ከጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ሰነዶች እንዲቀረቡለት የማዘዝ ወይም ሰነዱ ባለበት ቦታ ሄዶ የማየትና ሌሎች ለምርመራ ተግባሩ አስፈላጊ የሆኑ እርምጃዎች መውሰድ ይችላሉ፡፡

16. **የስብሰባ ስነ ስርዓት**

1. ኮሚቴው በ15 ቀን አንድ ጊዜ ወይም በዩኒቨርሲቲው የስርዓተ-ጾታ ክፍል የቀረቡ አቤቱታዎችን አስቸኳይነት መሠረት በማድረግ በሚያቀርበው ጥያቄ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
2. ኮሚቴው የሚያቀርበው የውሣኔ ሀሣብ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፤ ድምጹ እኩል በኩል የተከፈለ እንደሆነ የሰብሳቢው/ዋ ወይም ሰብሳቢው/ዋ በማትኖርበት ጊዜ በሰብሳቢው/ዋ የተወከለ/ች ሰብሳቢ ያለበት ወገን ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፡፡
3. የኮሚቴው ምልዓተ ጉባኤ አራቱ አባላት ከተገኙ ጉባኤው ይሟላል፤ የስብሰባ ስነ ስርዓቱን በሚመለከት በልምድ ተቀባይነት ያላቸውን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓቶች ይከተላል፡፡
4. የኮሚቴው ሰብሳቢ በማትኖርበት /በማይኖርበት/ ጊዜ በሰብሳቢዋ/ው በጽሁፍ የተወከለ ሌላ አባል ስብሰባውን ሊመራ ይችላል፡፡ ሆኖም ሰብሳቢዋ/ው በጽሁፍ ያልወከች/ለ ከሆነና ከአምስት የስራ ቀናት በላይ የማትገኝ /የማይገኝ/ ከሆነ ሌላ እስክትመለስ /እስኪመለስ/



F.D.R.E Ministry Of Education

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፒ/ር)
ፕሬዝዳንት

ስብሳቢ በአባላቱ መመረጥ አለበት፡፡ ይህ ሰብሳቢዋ/ው ራሷን/ራሱን/ በምታነሳበት /በሚያነሳበት/ ጊዜም ይፈፀማል፡፡

5. በኮሚቴው የሚጣሩ አቤቱታዎች የመጨረሻ ውሣኔ አግኝተው በማስታወቂያ ሰሌዳ እስኪለጠፉ ድረስ በሚስጥር መጠበቅ ይኖርበታል፡፡

## 17· የኮሚቴ አባላት መከተል ስለሚገባቸው የሥነ-ምግባር መርሆዎች

1. ማንኛውም የኮሚቴ አባል ለኮሚቴ አባልነት ያወቃቸውን ማንኛውንም ጉዳዮች በሚስጥር መጠበቅ አለባት/በት፡፡
2. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በውሣኔ የቀረቡ አቤቱታዎች ከራሷ/ሱ፣ ከቅርብ ጓደኛዋ/ው ወይም ከዘመዷ/ዱ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ባወቀ/ች ጊዜ በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ከአባልነት እራሷ/ሱን ማግለል አለባት/በት፡፡ እራሷ/ሱን የማታነሳ /የማያነሳ/ ከሆነም የኮሚቴው ሰብሳቢ ጉዳዩን ባወቀች/ቀ ጊዜ ሊያስነሳው ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ በኮሚቴ አባላቱ ገለልተኛነት ላይ ቅሬታ ያለው ጉዳዩ የሚመለከተው ሰው ገለልተኛ አይደለም የተባለው ሰው እንዲነሳለት ለኮሚቴው ሰብሳቢ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡ የኮሚቴው አባላት በሚነሱበት ጊዜ የኮሚቴው አባላት ከምልዓተ ጉባኤው በታች የሚሆን ከሆነ በአንቀጽ 13 ከተቀመጡት ጽ/ቤቶች ወይም ማህበራት የሚመረጥ የኮሚቴ አባል ከሆነ ምክትሉ ሊተካው ይገባል፡፡
3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል አቤቱታዎችን በሚያይበት ወቅት በፆታ፣ በዘር፣ በኃይማኖት፣ በፖለቲካ አመለካከት፣ በአካል ጉዳት ወይም በሌላ ሁኔታ መሠረት ያደረገ አድሎን መፈፀም አይኖርበትም፡፡
4. ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትንና ሌሎች በኮሚቴው የሚወሰኑ የስነ-ምግባር መርሆዎችን የጣሸ/ሰ ወይም በማናቸውም ሁኔታ የኮሚቴውን ስራ ያደናቀፈች/ፈ የኮሚቴ አባል ከአባልነቱ መሠረዟ/ዙ እንደተጠበቀ ሆኖ በዲሲኘሊን ጉድለት ተጠያቂ ትሆናለች/ይሆናል፡፡

## 18· የአቤቱታ አቀራረብ ስነ-ስርዓት

1. ማንኛውም የጾታዊ ትንኮሣና ጥቃት ተግባር ተፈፅሞብኛል የሚል ሰው አቤቱታውን ጉዳዩ ተፈፀመ ከተባለበት ጊዜ ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ለዩኒቨርሲቲው የስርዓተ ጾታ ጉዳይ ቢሮ በጽሁፍ ማቅረብ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም ግን በተጠቀሰው ጊዜ አቤቱታው ካልቀረበና ድርጊቱን የፈፀመው ተከሳሽ እርምጃ ካልተወሰደበት ተጠያቂ አይሆንም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አቤቱታ አቅራቢው በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ አቤቱታውን ማቅረብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑን በበቂ



F.D.R.E Ministry Of Education ... University

... በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

ማስረጃ ያረጋገጠ ከሆነ አቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜው የሚቆጠረው ከአቅም በላይ የሆነውን ምክንያት ከተወገደበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

3. አቤቱታ አቅራቢው በአካል አቤቱታውን ማቅረብ በማይችልበት ጊዜ በሕጋዊ መንገድ በወከለው ሰው አማካኝነት ማቅረብ ይችላል፡፡
4. ማንኛውም የስርዓተ ጾታ ትንኮሳና ጥቃትን በሚመለከት የሚቀርብ የአቤቱታ ማመልከቻ የሚከተሉትን መያዝ አለበት፤

ሀ) የከሳሽ ስምና የሚማመርበት የትምህርት ክፍል ወይም የሚሰራበት ክፍል፣

ለ) ድርጊቱ የተፈፀመበት ቀን፣ ቦታና ሰዓት፣

ሐ) ተፈፀመ የተባለው የወሲባዊ ትንኮሳ ዓይነት /የድርጊቱ መግለጫዎች፣

መ) የተከሳሹ ስምና የትምህርት ክፍል/የሥራ ቦታ ወይም ሌላ ማንኛውንም ዓይነት መለያ፣

ሠ) የምስክሮች ስም ዝርዝር፣

ረ) በአቤቱታ አቅራቢ እጅ የሚገኙ የጽሁፍ ወይም ሌሎች ማስረጃዎች ወይም በእጅ የማይገኙ ከሆኑ የሚገኙበትን ቦታ መጥቀስ፣

ሰ) የሚጠየቅ ዳኝነት፣

ሸ) የአቤቱታ አቅራቢ ፊርማና አቤቱታ የቀረበበትን ቀን መያዝ ይኖርበታል፡፡

5. የዩኒቨርሲቲው ስርዓተ ጾታ ጽ/ቤት ከላይ የተጠቀሱትን ዝርዝሮች የያዘ የአቤቱታ ማመልከቻዎች የሚቀርቡባቸው ቅጾች ማዘጋጀት አለበት፡፡

## 19. ለኮሚቴ አባላት፣ ለከሳሽና ለምስክሮች የሚደረግ ጥበቃ

ማንኛው የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በዚህ መመሪያ መሰረት ከሳሽ ወይም ምስክር ሆኖ ለቀረበ ወይም በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሰረት የኮሚቴ አባል ሆኖ ለተመደበ የአካዳሚክ ማህበረሰብ አባል ወይም አስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ተገቢውን ጥበቃ እንዲያገኙ ያደርጋል፡፡

## 20. አቤቱታ ማቅረብ ስለማይቻልባቸው ሁኔታዎች

1. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) የተጠቀሰው የአቤቱታ ማቅረቢያ ጊዜ ያለፈ እንደሆነ፣
2. ቀደም ሲል ጉዳዩ በዚሁ አካል የመጨረሻ ውሣኔ የተሰጠበት ከሆነ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃትን በሚመለከት አቤቱታ ማቅረብ አይቻልም፡፡

F.D.R.E Ministry Of Education ... University



ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፐ/ር)
ፐሬዝዳንት

21. **አቤቱታ የቀረበበት ሰው የመደመጥ መብት**

1. ማንኛውም በወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት ተግባር አቤቱታ የቀረበበት ሰው የቀረበበትን አቤቱታ የማወቅ፣ ራሱን የመከላከልና የመደመጥ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
2. የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴው የቀረበውን አቤቱታ ከቀጠሮ 10 ቀናት በፊት አቤቱታ ለቀረበበት ሰው እንዲደርሰው ማድረግ አለበት፡፡

22. **የዲሲኘሊን እርምጃ አወሳሰድ**

1. በዩኒቨርሲቲው የአካዳሚክ ማህበረሰብን በሚመለከት በአካዳሚክ ሠራተኞች የዲሲፕሊን አፈፃፀምና ስነ-ምግባር ደንብ ወይም በተማሪዎች የስነ-ምግባር ደንብ ስር የተቋቋመው የዲሲፕሊን ኮሚቴ ያለው አሰራር እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም በዩኒቨርሲቲው፣ ተማሪዎችና መምህራን የሚፈፀም ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃትን በተመለከተ በዚህ መመሪያ አንቀጽ 13 መሠረት የተቋቋመው የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት አጣሪ ኮሚቴ ጉዳዩን አጣርቶ የውሣኔ ሀሣብ ይሰጣል፡፡
2. ጾታዊ ትንኮሳና ጥቃትን በሚመለከት ኮሚቴው አቤቱታ በቀረበለት በ20 ቀናት ውስጥ ጉዳዩን አጣርቶ የውሣኔ ሀሣቡን ለአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ወይም ለአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት ማቅረብ አለበት፡፡
3. የአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ወይም የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት ኮሚቴው የውሣኔ ሀሣቡን ባቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡
4. የአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ወይም የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት ከኮሚቴው የቀረበለትን የውሣኔ ሀሣብ ለማጽናት ወይም ለመሻር ወይም ለማሻሻል ወይም ከኮሚቴው የውሣኔ ሀሣብ የተለየ ውሣኔ ለመስጠት ይችላል፡፡
5. በጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት የዩኒቨርሲቲው ም/ፕሬዝዳንቶች ተከሳሽ ከሆኑ የውሳኔ ሀሳብ ለፕሬዝዳንቱ ቀርቦ ይወሰናል፡፡
6. ፕሬዝዳንቱ ተከሳሽ በሚሆንበት ጊዜ ኮሚቴው ጉዳዩን አጣርቶ ለትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ጾታ ማኔጅመንት የስራ ሂደት ያቀርባል፣ የስራ ሂደቱም ጉዳዩን አጣርቶ ለትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ ከውሳኔ አስተያየት ጋር ያቀርባል፡፡
7. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚቴው በአቤቱታዎች ላይ የውሳኔ ሀሳብ ከማቅረቡ በፊት የወሲባዊ ትንኮሳውና ጥቃት እንዲቆም የሚያደርጉ ጊዜያዊ ትዛዞች ሊሰጥ ይችላል፡፡

በኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር እንጅባራ ዩኒቨርሲቲ F.D.R.E Ministry Of Education Injibara University

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ዶ/ር)
ፕሬዝዳንት

8. በዚህ መመሪያ መሠረት የሚሰጡ ማናቸውም ዓይነት ውሣኔዎች አቤቱታ አቅራቢውን ጉዳዩ በሌሎች ህጎች የተቀመጡ መደበኛ የፍርድ ሂደቶችን እንዳይከተል አያግዱትም።

23. ይግባኝ

በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ ቁጥር 1064/2010 ለአስተዳደርና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች የተቀመጠው የይግባኝ መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በወሲባዊ ትንኮሳና ጥቃት የተከሰሰና የዲሲፕሊን እርምጃ የተወሰደበት ወይም የተቀጣ ማንኛውም የዩቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል በአስተዳደርና ልማት ጉዳዮች ም/ፕሬዝዳንት ወይም በአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት የቅጣት ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ማቅረብ ይችላል። ፕሬዝዳንቱ ይግባኙ በቀረበለት በ10 ቀናት ውስጥ ይግባኙን መርምሮ ውሣኔ መስጠት አለበት።

24. የቅጣት ሪኮርድ መቆያ ጊዜ

1. ቀላል ትንኮሳ የፈፀመና የተቀጣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል የጥፋት ድርጊቱን ከፈፀመበት ቀን ጀምሮ ለሁለት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል።
2. ከባድ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት የፈፀመና የተቀጣ የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ አባል ለአምስት አመት የጥፋት ድርጊቱ በሪኮርድነት ይጠቀስበታል።

25. ከስራ አግዶ ስለማቆየት

1. አቤቱታ የቀረበበት ሰው ፈፀመ የተባለው ድርጊት ከባድ ፆታዊ ትንኮሳ እና ጥቃት ከሆነ እና የግለሰቡ መኖር በዩኒቨርሲቲው ሆነ በሌሎች ላይ ከፍተኛ ችግር ያደርሳል ብሎ ካሰበ የአስተዳደርና ልማት ም/ፕሬዝዳንት ወይም የአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ኘሬዝዳንት ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ከስራ እና ከደሞወዝ ሊያግደው ይችላል።
2. አቤቱታ የቀረበበት ሰው ከስራ እንዲሰናበት ካልተወሰነበት በስተቀር ሳይከፈለው የቀረው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል።

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

26. ስለሌሎች ሶስተኛ ወገኖች

የተለያዩ ስራዎች ለመስራት ከዩኒቨርሲቲው ጋር ውል የሚገቡ የስራ ተቋራጮች ወይም ግለሰቦች በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በሚቆዩበት ጊዜ በዚህ መመሪያ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን እንዳይተላለፉ በሚገቡት ግዴታ ላይ እንዲካተት መደረግ አለበት።

F.D.R.E Ministry Of Education



ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት

27. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም የእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ የጾታዊ ትንኮሳና ጥቃት መፈፀሙን ባወቀ ጊዜ ሪፖርት የማድረግ፣ለምስክርነት ሲጠራ የመቅረብ፣ በእጅም ሆነ በስራ ኃላፊነቱ የሚገኙ መረጃዎችን በመስጠት የመተባበር ኃላፊነት አለበት።

28. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት የተጀመሩ የወሲብ ትንኮሳ ክሶች ካሉ ቀደም ሲል በተጀመረበት ሁኔታ ተጣርተው ውሣኔ ያገኛሉ።

29. <u>ተፈፃሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

ይህን መመሪያ የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም የአሠራር ልምዶች ይህ መመሪያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊነታቸው ይቋረጣል።

30. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በእንጅባራ ዩኒቨርሲቲ ሴኔት ከፀደቀበት ከግንቦት/2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ብርሃኑ በላይ አቡኔ (ፕ/ር)
ፕሬዝዳንት